የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ — ጥር ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No. 3
ADDIS ABABA – 6th February, 1996

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፲፭/፲፱፻፹፰ ዓ·ም·
"ለኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ፕሮጀክት ከፊል ማስፈጸሚያ ከአውሮፓ ኢንቬስትመንት ባንክ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ........ ገጽ ፺፪

## CONTENTS

Proclamation No. 15/1996
European Investment Bank Loan Agreement for partly financing the Ethiopian Civil Aviation Authority Project Ratification Proclamation ........ Page 92

### አዋጅ ቁጥር ፲፭/፲፱፻፹፰

### በኢትዮጵያ መንግሥትና በአውሮፓ ኢንቬስትመንት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለአዲስ አበባ ቦሌ አይሮፕላን ማረፊያ እና በክልሎች ለሚገኙ ፮ (ስድስት) አይሮፕላን ማረፊያዎች ማሻሻያና ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ፕሮጀክት ፣ ከፊል ማስፈጸሚያ የሚውል ፳፩ (ሃያ አንድ) ሚሊዮን ኢ·ሲ·ዩ· የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ መንግሥትና በአውሮፓ ኢንቬስትመንት ባንክ መካከል ታህሳስ ፩ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም· በሉክሰምበርግ ስለተፈረመ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት ማፅደቅ በማስፈለጉ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ፕሮጀክት ከፊል ማስፈጸሚያ ከአውሮፓ ኢንቬስትመንት ባንክ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፲፭/፲፱፻፹፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

### PROCLAMATION NO. 15/1996

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE EUROPEAN INVESTMENT BANK

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the European Investment Bank stipulating that the European Investment Bank provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of twenty-one million European Currency Units (ECUs 21,000,000) for partly financing the Ethiopian Civil Aviation Authority Project comprising the extension and rehabilitation of the Addis Ababa Bole Airport and the rehabilitation of Six Regional Airports, was signed in luxembourg, on the 11th day of December, 1995;

WHEREAS, it is necessary to ratify, said Loan Agreement;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constituton, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "European Investment Bank Loan Agreement for partly financing the Ethiopian Civil Aviation Authority Project Ratification Proclamation No. 15/1996."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price } 1·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

## ፪· <u>የብድር ስምምነቱ መጽደቅ</u>

ከዚህ በላይ የተመለከተውን ፕሮጀክት በከፊል ለማስፈጸም የተደረገው የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል ።

## ፫· <u>የገንዘብ ሚኒስትር ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስትሩ የብድሩን ገንዘብ ፳፩ (ሃያ አንድ) ሚሊዮን ኢ·ሲ·ዩ በብድሩ ስምምነት በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

## ፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥር ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ፣ ጥር ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 2. *Ratification of the Loan Agreement*

The Loan agreement for partly financing the project here in above specified is here by ratified.

## 3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utililization of the loan amount of twenty-one million European Currency Units (ECUs 21,000,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 6th day of February, 1996.

Done at Addis Ababa, this 6th day of February, 1996.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ ፡፡
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE